# ወረርሽኝ (ፕሌግ)

## ወረርሽኝ ምንድን ነው?

ወረርሽኝ በአንድ የረቂቃን ነፍሳት ዓይነት ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። በተፈጥሮ በሽታው ከአይጠ መጎጥ ወደ ሰው የሚተላለፈው በቁንጫ ንክሻ ነው። በአሥራ አራተኛው ክፍለዘመን ይህ በሽታ በሶስት የተለያዩ ጊዜያት በዓለም ላይ ተራብቷል። በሽታው በገባበት ቦታም ላይ የሕዝቡን ከአንድ ሶስተኛ እስከ ግማሽ የሚሆን ገድሏል።



*በወረርሽኝ የተበከለች ቁንጫ*

የጽዳትና የኑሮ ሁኔታቸዎች ግን ስለተሻሻሉ ወረርሽኝ በሽታ አሁን ብዙ አይገኝም። ሆኖም በዓለም ላይ በአሁኑ ጊዜ እስከ 2000 የሚሆኑ በሽተኞች የገኛሉ - ከነዚህም ወደ 15 የሚሆኑት በደቡብ ምዕራብ አሜሪካ ይገኛሉ።

ሶስት ዓይነት የወረርሽኝ በሽታዎች አሉ፥

- **ቡቦኒክ ወረርሽኝ** በተፈጥሮ የተለመደው ዓይነት ወረርሽኝ ሲሆን ከ 75 እስከ 97 በመቶ የሚሆኑት በሽተኞች ይህንን ዓይነቱ ወረርሽኝ ነው የሚይዛቸው። በቶሎ የሚታዩት ምልክቶቹ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ድካምና የሚያሙ ያበጡ እጢዎች ወይም "ቡቦዎች" ተብለው የሚታወቁት ናቸው።
- **ሴፕቲሴሚክ ወረርሽኝ** - ይህ በወረርሽኝ ረቂቃን ነፍሳት የሚመጣ የደም መበከል የተለመደ አይደለም። በተፈጥሮ ከሚመጡት የወረርሽኝ ታማሚዎች 20 በመቶውን የሚይዝ ነው።
- **ኑሞኒክ ወረርሽኝ** ከሁሉም በላይ በጣም አስጊው የወረርሽኝ ዓይነት ሲሆን በተፈጥሮ ግን ከሁሉም በታች ያልተለመደው ነው። ከበሽተኞች ሁሉ ከ14 በመቶ ያነሰ የሚይዝ ነው። ሆኖም በሽብር ጥቃት በኩል ይመጣል ተብሎ የሚታመነው ይህ ዓይነቱ ወረርሽኝ ነው። በሽታው የሚከሰተው ረቂቃን ነፍሳቱ ሳንባ ውስጥ ሲገቡና ኃይለኛ ዓይነት የሳንባ ምች በቶሎ ሲያከትሉ ነው።

የሳንባ ወረርሽኝ ምልክቶቹ ከፍተኛ ትኩሳት፣ የደረት ሕመም፣ ሳል፣ የትንፋሽ ማጠርና ሲስሉ ከደም የተቀላቀለ ፈሳሽ ወይም ንፍጥ መውጣት ናቸው። በ24 ሰዓት ውስጥ የአንቲባዮቲክ ሕክምና ካልተጀመረ በሽተኛው ሊሞት ይችላል። በሽተኞቹ አስቸኳይ ሕክምና ካላገኙ የመሞት ዕድላቸው 100 በመቶ አካባቢ ነው።

የሳንባ ወረርሽኝ ምልክቶች የሚታዩት ለበሽታው ከተጋለጡ ከአንድ እስከ ሁለት ቀን በኋላ ነው።

## ወረርሽኝ የሚይዘው እንዴት ነው?

ሰዎች የቡቦኒክ ወረርሽኝ የሚይዛቸው ከተበከሉ እንስሶች ነው። ረቂቃን ነፍሳቱ የሚዛመቱት በተበከሉ ቁንጫዎች ንክሻ፣ የተበከሉ እንስሶች ሲነክሱ ወይም ሲቧጭሩ ወይም ከተበከሉ የእንስሳ ሬሳ ጋር መነካካት ሲኖር።

ሰዎች ኑሞኒክ ወረርሽኝ የሚይዛቸው የወረርሽኝ ረቂቃን ነፍሳት የያዘ ጠብታ ሲተነፍሱ ነው። እነዚህ ጠብታዎች አየር ውስጥ የሚገኙት የታመሙ ሰዎች ወይንም እንስሶች በሚስሉበት ጊዜ ነው። ሆኖም ወረርሽኝን እንደ ጦር መሣሪያ የሚጠቀሙበት ረቂቃን ነፍሳቱን አየር ላይ አውቆ በመልቀቅ ነው።

## ከሌላ ሰው ሊይዝ ይችላል?

አዎን - በሽታው የያዛቸው ሰዎች ሲስሉ አየር ላይ የሚበትኑትን ጠብታዎች በመተንፈስ በሽታው ሊይዝ ይችላል።

## የሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታመነው ለምንድን ነው?

የወረርሽኝ እንደ መሣሪያ መጠቀም መቻል ቢያንስ ለአለፉት 60 ዓመታት ሲጠና ቆይቷል። እንደሚባለው ከሆነ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Communications Office
625 North Robert Street/Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-4989
www.health.state.mn.us

ጃፓናዊዎች የተበከሉ ቁንጫዎችን እንደ ቦምብ ለመጠቀም ሞክረው ነበር። በ1950ዎቹ ዓ.ም. እና በ1960ዎቹ ዓ.ም. አሜሪካም የቀድሞው ሶቪዬት ዩኒየንም የወረርሽኝ ረቂቃን ነፍሳትን አየር ውስጥ የመልቀቂያ ዘዴ አበጅተው ነበር።

ወረርሽኝ የሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታመነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፦

- ረቂቃን ነፍሳቱን አየር ላይ ለቆ ብዙ ሰዎችን መበከል ይቻላል።
- አየር ላይ የተለቀቁት ረቂቃን ነፍሳት አደገኛውን ኑሞኒክ ወይም የሳንባ ወረርሽኝን ያስከትላል።
- ኑሞኒክ ወረርሽኝ ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፍ ስለሚችል በሽታው ሊባዛ ይችላል።
- ኑሞኒክ ወረርሽኝ አደገኛ በሽታ ሲሆን የመግደል ኃይሉ ከፍተኛ ነው።
- የኑሞኒክ ወረርሽኝ በሽታ ቢመጣ ኃይለኛ ፍርሃትና ሽብር ይፈጥራል።

የኑሞኒክ ወረርሽኝ የመጀመሪያ ምልክቱ ከጥቃቱ ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ ብዙ ሰዎች ኃይለኛ የመተንፈስ ችግር አጋጥሟቸው ሕክምና ሲፈልጉ ሲታይ ነው። በዚህን ጊዜ ረቂቃን ነፍሳቱ አየር ውስጥ አይገኙም። ለረቂቃን ነፍሳቱ የተጋለጡት ሰዎች አስቸኳይና ጥብቅ ሕክምና ካላገኙ አብዛኞቹ ይሞታሉ።

## ወረርሽኝን መከላከል ይቻላል?

በአሁኑ ጊዜ ለወረርሽኝ የሚሠጥ ምንም ዓይነት ክትባት ባይኖርም ለመሥራት ሙከራ እየተደረገ ነው። ሰዎች ለታመሙ ሰዎች ወይም ለእንስሶች ሲጋለጡ አንቲባዮቲክ በመጠቀም በሽታውን መከላከል ይቻላል - ይህ የሚሠራው ሕክምናው ወዲያው ከተጀመረ ነው።

አየሩ ውስጥ የተለቀቁ ረቂቃን ነፍሳት በሕይወት የሚቆዩት ከአንድ ሰዓት ያነሰ ጊዜ ነው። የፀሐይ ብርሃን፣ ሙቀትና መድረቅ ይገድላቸዋል። ለበሽታው ከተጋለጡ በኋላ እስከ አንድ ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ልብስዎን አውልቀው ገላዎን ከታጠቡ የመታመምዎን ዕድል ይቀንሳሉ። ሆኖም ከበሽታው ለመከላከል ግን አንቲባዮቲክ መውሰድ ይኖርብዎታል።

## ሊታከም ይችላል?

የወረርሽኝ በሽታ ዓይነቶች በሙሉ በአንቲባዮቲክ ሊታከሙ ይችላሉ። ሆኖም የሳንባ ወረርሽኝ የያዛቸው ሰዎች ምልክት ማሳየት ከጀመሩ እስከ 24 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ሕክምና መጀመር አለባቸው። ሕክምና ካልጀመሩ የሳንባ በሽታው በአብዛኛው ለሞት የሚያደርስ በሽታ ነው።

## ለወረርሽኝ የተጋለጥኩ ከመሰለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

ለወረርሽኝ ተጋልጠው ከሆነ ላያውቁት ይችላሉ። ሆኖም ተጋልጫለሁ ብለው የሚያምኑ ከሆነ ዶክተርዎን በአስቸኳይ ያነጋግሩ። በአካባቢዎ ጥርጣሬ የሚያሳድር እንቅስቃሴ ካዩ - ማለትም የበሽታውን ጀርሞች እንደ ጦር መሣሪያ ለመጠቀም የሚሞክር ካዩ - በአካባቢዎ ለሚገኘው የሕግ አስከባሪ ድርጅት ያሳውቁ።